



# የእናትነት ዋስትና

**የእናትነት «ቢቱዋኽ» የታለመው ለወላዷ እና ለሚወለደው ሕጻን መሠረታዊ የሆኑ ጥቅሞችን ለማስከበር እና ወላዷ በእርግዝና እና በመውለዷ ምክንያት ለሚመጣው የገቢ መቋረጥ ካሳ መስጠት ነው።**

## የሆስፒታል መተኛ ክፍያ

ቢቱዋህ ሌኡሚ ለወላዷ ማስተኛ የወጡትን ወጪዎች **ለሆስፒታሉ** የሚከፍለው ክፍያ ነው።

## የወሊድ ስጦታ/ክፍያ

በወሊድ ምክንያት ለምትከፍላቸው የመጀመሪያዎቹ ወጪዎች ላይ ለመሳተፍ ሲባል ለወላዷ የሚከፈላት ገንዘብ ነው። ክፍያው በአንድ ወር ውስጥ የልጆች ክፍያ ለሚከፈልበት የባንክ ሒሳብ ቁጥር የሚተላለፍ ሲሆን የመጀመሪያዋ ወሊድ ከሆነ ግን በወለደችበት ሆስፒታል ለሰጠችው የሒሳብ ቁጥር ይከፈላታል።

### የሆስፒታል መተኛ ክፍያ እና የወሊድ ስጦታ/ክፍያ («ስጦታ ለይዳ») መብት ያለው ማን ነው?

ሆስፒታል ውስጥ የወለደች ወይም ሆስፒታል የተኛች ወላድ ልክ ከወለደች በኋላ (ሕጻኑ በሕይወት የተወለደ ከሆነ ወይም የተወለደው ከ26 ሳምንታት እርግዝና በኋላ ከሆነ) እና ከሚከተሉት አንዷ የሆነች፦

- የእስራኤል አገር ኗሪ የሆነች ወይም የእስራኤል አገር ኗሪ ሰው ባለቤት የሆነች (ወሊዱ ከእስራኤል አገር ውጪም ቢሆን)።
- እስራኤል ሀገር ውስጥ የምትሠራ ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም የግል ሥራ ካላት (የእስራኤል ሀገር ኗሪ ባትሆንም ወሊዱ እስራኤል ውስጥ የተካሄደ ከሆነ)።
- ባለቤትዋ እስራኤል ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራ ወይም በግሉ የሚሠራ ሆኖ ልክ ከመውለዷ በፊት ቢያንስ ስድስት ወራት በተከታታይ የሠራ (ወላዷ እና ባለቤትዋ የእስራኤል አገር ኗሪዎች ባይሆኑም፣ ወሊዱ እስራኤል አገር የተካሄደ ከሆነ)።

### የሆስፒታል መተኛ ክፍያ እና የወሊድ ስጦታ/ክፍያ (እንዲሁም ለልጆች ክፍያ) ጥያቄ አቀራረብ

ወሊድ በተካሄደበት ሆስፒታል አማካኝነት ለቢቱዋህ ሌኡሚ ይቀርባል። ለዚህም ሲባል ወላዷ የራሷን እና የባለቤቷን መታወቂያ ማምጣት እንዲሁም የራሷን የባንክ ሒሳብ ቁጥር (ወይም የእሷን እና የባለቤቷን የጋራ የሒሳብ ቁጥር) ለሆስፒታሉ ማቅረብ አለባት።

### በጥር 2014 ያለ የወሊድ አጠቃላይ ስጦታ/ክፍያ ("ማዓናክ ለይዳ")፦

ለቤተሰብ የመጀመሪያ ልጅ 1751 ሼቄል
ለቤተሰቡ ሁለተኛ ልጅ 788 ሼቄል
ለሦስተኛ ልጅ ወይም ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ልጅ 525 ሼቄል
ለመንትዮች 8757 ሼቄል
ለሦስት 13136 ሼቄል

> በአንድ ጊዜ ከሁለት ልጆች በላይ የወለደች ወላድ ለወሊድ ልዩ ("ኪጽቫት ለይዳ") ክፍያም ባለ መብት ናት (ዝርዝሮቹ በቀጣዩ ክፍል ይቀርባሉ)።

## የወሊድ ክፍያ ("ድሜይ ለይዳ")

"ድሜይ ለይዳ" የሚከፈለው ለወሊድ እረፍት ለወጣች የምትሠራ ሴት ሲሆን በዕረፍቷ ወቅት በወላዷ የሒሳብ ቁጥር አንድ ጊዜ ይከፈላል፤ ይህ ክፍያ የሚከፈለው ወላዷ በእርግዝና እና በመውለዷ ምክንያት ገቢዋን በማጣቷ ለመካስ ሲባል ነው።

### ለወሊድ ክፍያ ("ድሜይ ለይዳ") መብት ያለው ማን ነው?

- እስራኤል ሀገር ውስጥ የምትሠራ ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኛ (የእስራኤል ሀገር ኗሪ ባትሆንም)።
- ከእስራኤል ሀገር ውጭ በልዩ ሁኔታ ተቀጥራ የምትሠራ ተቀጣሪ ሠራተኛ።
- የ18 እና ከዚያን በላይ ዕድሜ ያላት በሞያ ሥልጠና ትምህርት ወይም በሞያ ማሻሻያ ትምህርት ላይ ያለች ሴት – በልዩ ሁኔታዎች።

### የወሊድ ክፍያ ("ድሜይ ለይዳ") መሥፈርቶች

- ለወላዷ "ከሚወስነው ቀን" ቀድሞ (ሥራዋን አቁማ በወሊድ እስከሚጠናቀቅበት ቀን ድረስ) ከ14 ወራት ውስጥ የ10 ወራት ወይም ከ22 ወራት ውስጥ የ15 ወራት የ"ቢቱህ ሌኡሚ" ክፍያ ለወላዷ ተከፍሎላት ከሆነ – የ14 ሳምንታት የ"ድሜይ ለይዳ" መብት አላት።
- ለወላዷ "ከሚወስነው ቀን" ቀድሞ (ሥራዋን አቁማ በወሊድ እስከሚጠናቀቅበት ቀን ድረስ) ከ14 ወራት ውስጥ የ6 ወራት የቢቱዋህ ሌኡሚ ክፍያ ለወላዷ ተከፍሎላት ከሆነ – የ7 ሳምንታት "የድሜይ ለይዳ" መብት አላት።

### እነዚህ ወራት "ከሚወስነው ቀን" ቀድመው ያሉ ከሆኑ የዋስትና ክፍያዎች እንደተከፈለባቸው ወራት ይቆጠራሉ ፦

- ሴትየዋ ሠርታ ከአሠሪዋ ደሞዝ የተቀበለችባቸው ወራት (የሕመም ክፍያን እና የዕረፍት ክፍያን ጨምሮ) ወይም የግል ሥራ ኖሯት ከገቢዋ ላይ የቢቱዋህ ሌኡሚ ክፍያ የከፈለችባቸው ወራት።
- ሴትየዋ ከቢቱዋህ ሌኡሚ "ድሜይ ለይዳ" (ለቀደመው ወሊድ) ወይም የሥራ ላይ ጉዳት ክፍያ ወይም የሥራ አጥ ክፍያ ወይም የአደጋ ክፍያ ወይም የእርግዝና መንከባከብ ክፍያ ወይም የሥራ የ100% የአካል መጉደል ክፍያ የተከፈለባቸው ወራት።
- ሴትየዋ የሕመም ክፍያ ወይም ከ"ኩፓት ጊሜል" የዓመት ፈቃድ የወሰደችባቸው ወራት።
- የያለክፍያ ዕረፍት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት (ለእነዚህ ወራት አሠሪዋ የቢቱዋህ ሌኡሚን ክፍያ ሊከፍል ይገባዋል)።
- ሴትየዋ በሞያ ማሰልጠኛ የተማረችባቸው ወራት እና "ከወሳኙ ቀን" በፊት ቢያንስ ለ30 ተከታታይ ቀናት ከሠራች።
- የውትድርና አገልግሎት ወራት – የውትድርና አገልግሎቷን አቋርጣ መሥራት ለጀመረች – በተወሰኑ መስፈርቶች።

> ከወሩ ቀናት በከፊሎቹ ከተሠራ ሙሉውን ወር እንደተሠራ ይቆጠራል።

### የወሊድ ክፍያ "ድሜይ ሃለይዳ" መጠን

"ቢቱዋህ" የሚከፈልበት 100% ደሞዝ ሆኖ "ማስ ሃክናሳ"፣ የቢቱዋህ ሌኡሚና የጤና ክፍያ ከተቀነሱ በኋላ እስከ ከፍተኛ የወሊድ ክፍያ "ድሜይ ለይዳ" (በጥር 2014 ለተቀጣሪ ሠራተኛ እና ለግል ሠራተኛ በቀን 1459.50 ነው)።

### የወሊድ እረፍትን ማራዘም

አንዲት ወላድ መንትዮችን (ከአንድ ሕጻን በላይ) በመውለዷ ምክንያት ወይም ሆስፒታል እሷ ወይም የተወለደው ሕጻን በሆስፒታል ውስጥ ቢያንስ ለ15 ቀን በመተኛታቸው ምክንያት የወሊድ ዕረፍቷን የማራዘም ወይም የመከፋፈል መብት አላት። ስለ ዕረፍቱ መራዘም ወይም ስለመከፋፈሉ በተቻለ ቅድሚያ ለቢቱዋህ ሌኡሚ ማሳወቅ የወላዷ ፋንታ ነው። ተጨማሪ መረጃ በቢቱዋህ ሌኡሚ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።

### የወሊድ ክፍያ አጠያየቅ እንዴት ነው?

የ"ድሜይ ለይዳ" መጠየቂያ ቅጽ የሆነውን 355/בל መሙላት እና በመኖሪያ አካባቢ ለሚገኝ የቢቱዋህ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ መስጠት። ቅጹን ከማንኛውም የቢቱዋህ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ መውሰድ ወይም ከቢቱዋህ ሌኡሚ ድርጅት የኢንተርኔት ድረ-ገጽ ማውረድና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ። ተቀጣሪ ሠራተኛ የሆነች ቅጹን ከአሠሪዋ መውሰድ ትችላለች።



# በቢቱዋህ ሌኡሚ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ

ቢቱዋህ ሌኡሚ ማመልከቻህን ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ይህንን የቢቱዋህ ሌኡሚ ውሳኔ በመቃወም ለአካባቢ የሥራ ጉዳይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ መብት አለህ። ይህን አቤቱታ ውሳኔውን ከሰማህበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 12 ወራት ድረስ ማቅረብ ትችላለህ።

## በአካባቢው የሚገኙ የሥራ ጉዳይ ፍርድ ቤቶች

| ከተማ | አድራሻ | ቴሌፎን |
|---|---|---|
| ኢየሩሳሌም | ቤት ሀድፋስ 20 | 02-6546444 |
| ቴል አቪቭ | ረሆቭ ሾከን 25 | 03-5128222 |
| ሐይፋ | ረሆቭ ፓል ያም 12 ፣ ሂኻል ሀሚሽፓት | 04-8698000 |
| ናጼሬት ኢሊት | ኪርያት ይስሐቅ ራቢን፣ ሂኻል ሀሚሽፓት | 04-6087777 |
| ቤርሼባ | ረሆቭ ሀቲክቫ 5፣ ሂኻል ሀሚሽፓት | 08-6470444 |

የአካባቢው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ኢየሩሳሌም ለሚገኘው አገር አቀፍ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል።

## አገር አቀፍ የይግባኝ ፍርድ ቤት

| | | |
|---|---|---|
| ኢየሩሳሌም | ኪርያት ሀየሶድ 20 | 077-2703333 |

## የፍርድን ሂደት በተመለከተ የሚሰጥ እርዳታ

የቢቱዋህ ሌኡሚን ውሳኔ ባለመቀበል ለአካባቢ የሥራ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ወስነህ ከሆነ፣ ከፍርድ ቤቱ አጠገብ ከሚገኙት የእርዳታ ቢሮዎች ይግባኝ በማቅረብ የፍርድ እርዳታ በነፃ ለመቀበል መብት አለህ። ጥያቄህን ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በመሙላት በመኖሪያ አካባቢህ በሚገኘው የእርዳታ ቢሮ ማቅረብ ይኖርብሀል።

## ለፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ እርዳታ የሚሰጡ ቢሮዎች

| ክልል | አድራሻ | ቴሌፎን |
|---|---|---|
| ኢየሩሳሌም* | ረሆቭ ሀሶሬግ 1፣ ቤት ሚጽፔ | 1-700-70-60-44 |
| ቴል አቪቭና ማዕከላዊ ክፍል | ሄንሪየታ ሶልድ 4 | 1-700-70-60-44 |
| ሐይፋና ሰሜኑ ክፍል | ሽደሮት ፓል ያም 15 አ ኪርያት ሀሜምሻላ | 1-700-70-60-44 |
| ቤር ሼባ | ሽደሮት ሻዛር 33፣ ፖስታ ሣ. ቁ 534.) ባይት ኖዓም) | 08-6404526 |
| ናጼሬት | ረሆቭ ቶፊክ ዛይድ፣ ብንያን ቫፋ ሰንቴር፣ 5ኛ ፎቅ | 1-700-70-60-44 |

* የኢየሩሳሌም ቢሮ የአሽቄሎን፣ የቅርያት ጋት፣ የአሽዶድና የኤይላት ኗሪዎችንም ጭምር ያገለግላል።

# የቢቱዋህ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች

## ዋነኛ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች

**ዋናው መሥሪያ ቤት ስደሮት ቫይጽማን 13፣ ኢየሩሳሌም**
ፋክስ – 02-6514002

**አሽዶድ** | ረኾቭ ሀባኒም 14
ፋክስ – 08-8686603

**አሽቄሎን** | ረሆቭ ሀናሲ 101
ፋክስ – 08-6740681

**ቤር ሼቫ** | ረኾቭ ሻዛር 31א

**ብኔ ብራክ** | ረኾቭ አሃሮኖቪች 12
ፋክስ – 03-6152976

**ኻዴራ** | ረኾቭ ሂሌል ያፌ 7א
ፋክስ – 04-6328108

**ሆሎን** | ፒንዘ ስ ላ ን 26፣ ፒናት ባርካት
ፋክስ – 03-5022422

**ሐይፋ** | ስደሮት ፓል ያም 8
ፋክስ – 04-8134900

**ቲቬርያ** | ረኾቭ ሆፋይን 1
ፋክስ – 04-6738040

**ያፎ** | ረኾቭ ሀትኩማ 30
ፋክስ – 03-5127149

**ኢየሩሳሌም** | ረኾቭ ቤን ሲራ 22
| ረኾቭ ሽምዖን ቤን ሼታህ 4
ፋክስ – 02-6755566

**ክፋር ሳባ** | ረኾቭ ቫይትስማን 39
ፋክስ – 09-7401688

**ካርሚኤል** | ረኾቭ ናሲ እስራኤል 3
ፋክስ – 04-9907389

**ናሀሪያ** | ስዴሮት ቫይትስማን 62
ፋክስ – 04-9528103

**ናጼሬት** | ረኾቭ ሀማኽጸቦት 3
ፋክስ – 04-6027408

**ናታንያ** | ረኾቭ ሔርጼል 68
ፋክስ – 09-8602704

**ዐፉላ** | ረኾቭ ኡሲሺኪን 1
ፋክስ – 04-6526086

**ፔታኽ ቲክቫ** | ረኾቭ ሮችልድ 72

**ኪራዮት** | **ኪሪያት ያም** ረኾቭ አኺ ኢላት 50
ፋክስ – 04-8411942

**ሪሾን ለጽዮን** | ረኾቭ እስራኤል ጋሊሊ 7
ፋክስ – 03-9426714

**ረኾቮት** | ረኾቭ ዳኒ ማስ 11
ፋክስ – 08-9450737

**ራምሌ** | 11 Danny Mass St.
ፋክስ – 08-9254157

**ራማት ጋን** | ረኾቭ ሀሀሽሞናኢም 15
ፋክስ – 03-6751261

**ቴል አቪቭ** | ረኾቭ ይስሐቅ ሳዴ 17

## ትንንሽ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች

**ኤላት** | ረኾቭ ማዲን 12
የ"ኪጽባዖት" ፋክስ – 08-6341134.
የክፍያ ፋክስ – 08-6024736

**ቤት ሼሜሽ** | ረኾቭ ሀናሲ 3
ፋክስ – 02-8348199

**ባት ያም** | ረኾቭ ጃቦትንስኪ 2
ፋክስ – 03-5127080

**ዲሞና** | ረኾቭ ጃቦትንስኪ 1
የ"ኪጽባዖት" ፋክስ – 08-6553777
የክፍያ ፋክስ – 08-6262882

**ሔርጼሊያ** | ረኾቭ ቤን ጎሪዮን 22
ፋክስ – 09-9312459

**ሚግዳል ሀዔሜክ** | ረኾቭ ኒጻኒም 45
ፋክስ – 04-6545223

**ምሥራቅ ኢየሩሳሌም** | ረኾቭ ኢብን ባቱታ 5
ፋክስ – 02-6755633

**ምራር** | የፖስታ ሳጥን ቁጥር 484 ሚኩድ 14930
ፋክስ – 04-6785560

**ናጼሬት ኢሊት** | ረኾቭ ዓማል 1
ፋክስ – 04-6028187

**አኮ** | ረኾቭ ጊቦሬይ ሲናይ 4
ፋክስ – 04-9551690

**ጽፋት** | ረኾቭ ሀፓልማህ 100
ፋክስ – 04-6825102

**ቅርያት ጋት** | ስዴሮት ሀዓጽማኡት 64
ፋክስ – 08-8865439

**ቅርያት ማላኺ** | ረኾቭ ራሺ 2
ፋክስ – 08-9376626

**ቅርያት ሽሞና** | ረኾቭ ቴል ሐይ (ቢንያን ሀማሽቢር ለጻርካን)
ፋክስ – 04-6738058

**ስዴሮት** | ረኾቭ ቤን ይሁዳ 21
ፋክስ – 08-6892103

**ሽፋርዓም** | ረኾቭ ሀቴኤና 7፣ ኤዞር ሃታዓስያ
ፋክስ – 04-9868791

## አገልግሎት የሚሰጥባቸው ማዕከሎች፣

ኡም ኤል ፋኽም | ኦፋኪም | ኦር ይሁዳ | ኦር አኪቫ | ኤልአድ | አሪኤል | ቤት ኤል | ቤት ሽአን | ቤታር ዒሊት | ሀጾር ሀግሊሊት | ቲራት ሀካርሜል | ያቭኔ | የሁድ | ዮክኒዓም | የሩሐም | ያርካ | ሞዲዒን | ሞዲዒን ዒሊት | ማካቢም-ረዑት | ማዓሌ አዱሚም | ማዓሌ ኤፍራይም | ማዓሎት – ታርሺኻ | ሚጽፔ ራሞን | ነቲቮት | ኡስፊያ – ዒር ሀካርሜል | ዖፍራ | ዒሊ | ዓማኑኤል | ዓራድ | ፓርዴስ ሐና | ካጽሪን | ኪርያት ዓርባ | ኪርያት አታ | ኪርያት ሽሞና | ሮሽ ሀዓይን | ራሀት | ሾሃም | ታርዲዮን

በአገልግሎት ማዕከሉ የሕዝብ መቀበያ ሰዓቶችን ለማጣራት ወደ ቢቱዋህ ሌኡሚ ድረ-ገጽ የቅርንጫፎች ክፍል ("ማዖር ስኒፊም") ግቡ።

### > የሕዝብ አቤቱታ ማቅረቢያ ክፍል

ቅሬታዎች ካሏችሁና መሻሻል ያለባቸውን ነገሮች ለመጠቆም ከፈለጋችሁ የሚከተለውን አድራሻ ተጠቀሙ።
የሕዝብ አቤቱታ ማቅረቢያ ክፍል፡ ስዴሮት ቫይጽማን 13 ኢየሩሳሌም 91909
ስልክ 02-6709070
ከእሑድ እስከ ኀሙስ ከ13፡00 እስከ 15፡00 ሰዓት፣
ፋክስ፡ 02-6525038

**በግል ለማጣራት ለሚፈልጉ ሁሉ፣**

**> በሞኬድ ቴሌፎን *6050 ወይም 1-222-6050**
ከእሑድ አስከ ኀሙስ ከ8፡00-15፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ መደወል ይቻላል

**> የቢቱዋህ ሌኡሚ ድረ-ገጽ**
**www.btl.gov.il**
**በ"בירורים אישיים" ክፍል**

### > በዋና እና በቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ መቀበያ ቀናት

እሑድ፣ ማክሰኞና ሐሙስ ከ8፡00-12፡30 ማንኛውንም ቢቱዋህ ሌኡሚን በተመለከተ ጉዳይ መጠየቅ ይቻላል። (ናጼሬት ቅርንጫፍ፣ ሰኞ፣ ማክሰኞና ሐሙስ)

ማክሰኞና ረቡዕ ከ15፡00- 17፡00 ሰዓት፣ በሥራ ላይ ለደረሰ አካል ጉዳት፣ እናትነትን ፣ ልጆችን፣ ተጠባባቂ የውትድርና አልግሎትን፣ ዋስትናን እና ክፍያን በተመለከተ አገልግሎት ይሰጣል (ከቴል አቪቭ ቅርንጫፍ በስተቀር)።

**ቢቱዋህ ሌኡሚ ተቆራጭ የሚከፍልባቸው ጉዳዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀያየሩ ይችላሉ። በመሆኑም መብትህን ተግባራዊ ለማድረግ በምትመጣበት ጊዜ መብቶችህን ከአንዱ በሚከተለው መንገድ ማጣራት ትችላለህ። ለሞኬድ ስልክ ቁጥር *6050 በመደወል ወደ ቅርኝጫፍ መሥሪያ ቤቶች በመሄድ፣ አጠቃላይና የተሻሻለ መረጃዎች ወደያዘው የቢቱዋህ ሌኡሚ ድረ-ገጽ www.btl.gov.il በመግባት በማንበብ። እንደዚሁም በመኖሪያ አካባቢህ ወደሚገኘው የቢቱዋህ ሌኡሚ ቅርንጫፍ በመሔድም ዝርዝር መረጃዎችን መቀበል ትችላለህ።**



**የቢቱዋኽ ሌኡሚ ድርጅት**

*ያንተና የኔ ግላዊ ዋስትና*

www.btl.gov.il

በቢቱዋኽ ሌኡሚ ሕጎችና በድንጋጌዎቹ አንዳንድ ጊዜ ለውጦች ይኖራሉ። በመሆኑም መብቶችህን ተግባራዊ ለማድረግ በምትመጣበት ጊዜ መብቶችህን ለሞኬድ *6050 በመደወል አጣራ ወይም አጠቃላይና የተሻሻለ መረጃ የያዘውን የቢቱዋኽ ሌኡሚ ድረ-ገጽ ጐብኝ።

ለጥር 20014 ተሻሽሎ የወጣ ትንሽ መጽሔት

በመጽሔቱ ውስጥ አጠቃላይ ማብራሪያዎች ይቀርባሉ፣ ነገር ግን እንደሕጉ ሙሉና እርግጠኛ ትርጉም ሊታዩ አይገባም።
በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በተባእታይ ጾታ የተጻፈው ሁሉ ለአንስታይ ጾታም ያገለግላል።